የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 እና 4

ነ. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ላይ በሌሊት ወደ ጌታ የሚመጣው የሚመጣው ፈሪሳዊ ማን ነበር?
ሀ)ቀያፋ ለ) ኒቆዲሞስ ሐ)ሐና መ) በጥሊሞስ

2. ኒቆዲሞስ በሌሊት የሚመጣበት ምክንያት ምን ነበር?
ሀ)በመዐልት ቢመጣ 'መምህር ነኝ እያለ እስከዛሬ ትምህርት ሳይከታተል ኖሯል ' እንዳይባል
ለ)የሌሊት ልቡና ባካና አይደለምና ትምህርት እንዲረዳው
ሐ)አይሁድ ከምኩራብ እንዳይለዩት ፈርቶ
መ)ሁሉም

3. "ከ _____ እና ከ _____ ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።"
ሀ) ንፋስ፣ እሳት
ለ)ውኃ፣ መንፈስ ቅዱስ
ሐ)ውኃ፣ እሳት
መ)ውኃ፣ እሳት፣ መንፈስ ቅዱስ

4. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ላይ ጌታ ስቅለትን የመሰለው በምንድነው?
ሀ)በተሰቀለ መና
ለ)ሙሴ በምድረ በዳ በሰቀለው እባብ
ሐ)በሰማይ ወፎች ሙበረር
መ)መልሱ የለም

5. "በምድር ያለውን ስነግራችሁ ካላመናችሁኝ በሰማይ ያለውን ብነግራችሁ እንዴት ታምኑኛላችሁ?" ሲል የሚናገረው ስለምንድነው?
ሀ)ስለምድር አዕዋፍት እና በሰማይ እላሉ እንስሳት
ለ)ስለዳግማዊ ልደቱ እና ስለ ቀዳማዊ ልደቱ
ሐ)ስለመላእክት
መ)ሁሉም

6. ከሚከተሉ ውስጥ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ላይ ጌታ ከተመሰለባቸው ነገሮች ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ)ብርሃን ለ)ሙሴ የሰቀለው አርዌ ብርት ሐ)ሙሽራ መ)ሰናፍጭ

7. የመጥምቁ ዮሐንስ የመምህርነት ዘመን ምን ያህል ነበር?
ሀ) 3 ዓመት ለ) 6 ወር ሐ) ነ መንፈቅ መ) ለ እና ሐ

8. "ሰው ከሰማይ ካልተሰጠው በስተቀር እርሱ ራሱ ጸጋን ገንዘብ ሊያደርግ ምንም አይችልም። " ጸጋ የተባለች...
ሀ)ገንዘብ ለ)መምህርነት ሐ)ሰማያዊ ዕውቀት መ)ለ እና ሐ

9. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ጥምቀት ትክክል የሆነው የቱ ነው?
ሀ)ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ያጠምቅ ነበር
ለ)የጌታ ደቀመዛሙርት ሰዎችን ያጠምቁ ነበር
ሐ)መጥምቁ ዮሐንስ ሰዎችን ያጠምቅ ነበር
መ)ለ እና ሐ

10. "...የሚለምንሽ ማን እንደሆነ ብታውቂስ አንቺ ደግሞ በለመንሺው ነበር፤ እርሱም የሕይወትን ውኃ በሰጠሽ ነበር " ሲል ሳምራዊቷ ሴት ምን ብላ መለሰች?
ሀ)መቅጃ እንኳን የለኝም
ለ)ጉድጓዱ ጥልቅ ነው
ሐ)የሕይወት ውኃ ከወዴት ታገኛለህ
መ)ሁሉም

ነነ. ጌታ ሳምራዊቷን ሴት ውኃ የጠየቃት በየት ነበር?
ሀ)በሲካር
ለ)በሰማርያ ከተማ
ሐ)ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ በሰጠው የወይን ቦታ አቅራቢያ
መ)ሁሉም

ነ2. ጌታ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ላይ ከእርሱ ስለሚገኘው ውኃ ምሳሌነቱ ምንን ያሳያል?
ሀ)ጌታ ያስተማረውን ትምህርት፣ የሰጠውን ልጅነት የተቀበለ ጽምዓ ነፍስ እንደሌለበት
ለ)ጌታ የሰጠው ልጅነት የእርሱ (በተቀበለው ሰው) ምክንያት ሲሰጥ እንደሚኖር
ሐ)በምድር ላይ ጌታ ከሰው የሰወረው ወንዝ እንዳለ እና ከሱ የጠጣ ሰው እንደማይጠማ
መ)ሀ እና ለ

ነ3. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ላይ ሳምራዊቷ ሴት አስቀድሞ ስንት ባሎች ነበሯት?
ሀ) 4 ለ) 5 ሐ) 7 መ) ነ0

ነ4."ዛሬ አብሮሽ ያለው ግን ባልሽ አይደለም " የተባለበት ምክንያት ...
ሀ)ያላገባችው ሰው ጋር አብራ ትኖር ስለነበር
ለ)ገና ሽማግሌ የላከ ሰው ስለነበር

ሐ)እርሱንም ጋኔን እንዳይገድለው ፈርታ በጎረቤት ልብስ ቀለብ እየሰጠች ታኖረው ስለነበር
መ)ሀ እና ሐ

15. ሐዋርያት ጌታ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ሲነጋገር የተደነቁት ስለምንድነው?
ሀ)"ምሁራነ መጻሕፍት ያላመኑበትን ይህቺ ሴት ታምንብኛለች ብሎ ነው " ብለው
ለ)በትሕትናው ሴት፣ ወንድ፣ ታላቅ፣ ታናሽ አይለይም ብለው
ሐ)ውኃ አቅርባ ስታስተናግደው ስለነበረ
መ)ሀ እና ለ

16. ሳምራዊቷ ሴት ከጌታ ጋር ከተነጋገረች በኋላ ምን አደረገች?
ሀ)እንስራዋን ትታ ወደ ከተማ ገባች
ለ)"የሠራሁትን ሁሉ ነገረኝ" ብላ መሰከረች
ሐ)አብሯት የሚኖረውን ሰው ከቤቷ ልታስወጣ ሄደች
መ)ሀ እና ለ

17. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ላይ የጌታ መብል የተባለ ምንድነው?
ሀ)ሰማያዊ መና
ለ)ዓሣ እና እንጀራ
ሐ)የአብን ፍቃድ መፈጸም
መ)ከአጫጆች የሚተርፈው እህል

18. "ያልደከማችሁበትን እንድታጭዱ ላክኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ " ሲል ሌሎች የተባሉ እነማን ናቸው?
ሀ) መላእክት ለ) አጋንንት ሐ) ነቢያት መ) የሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት

19. ከሳምራዊቷ ሴት ምስክርነት በኋላ ሳምራውያን ጌታን በእነርሱ ዘንድ እንዲኖር ሲማልዱት ጌታ ምን አደረገ?
ሀ) ብዙ የሚያስተምረው ህዝብ በሌላ ቦታ ስላለ ተቻኩሎ ሄደ
ለ)ሁለት ቀን በዚያ ተቀመጠ
ሐ)አራሳቸው እየተከተሉት እንዲማሩ እንጂ እርሱ እንደማይቆይ ነገራቸው
መ)ሀ እና ሐ

20. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ላይ ልጁ ሊሞት የቀረው የንጉሥ ወገን የሆነው ሰው ጌታን ስለ ልጁ የለመነው በየት ነበር?
ሀ)ውኃን ወደ ወይን በቀየረባት በቃና
ለ)በቅፍርናሆም
ሐ)በገሊላ
መ)ሀ እና ሐ

21. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 4 ላይ የንጉሥ ወገን የሆነውን ሰው ልጅ ጌታ ከንዳዱ የፈወሰው በስንት ሰዓት ነበር?
ሀ) በ 6 ሰዓት ለ) በ 7 ሰዓት ሐ) በ9 ሰዓት መ) በ12 ሰዓት